የ 2012 ዓም የ 12 ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና የድጋሜ የምዝገባ ፕሮግራም

ተ/ቁ	የት/ቤቱ ስም	የተማሪ ብዛት	የምዝገባ ቀን	የምዝገባ ቦታ
1	ደራርቱ ቱሉ	428	18/02/2013	ደራርቱ ቱሉ
2	ገላን የወንዶች አዳሪ ት/ቤት	12	19/02/2013	ደራርቱ ቱሉ
3	ፊታውራሪ አባይነህ	147	20/02/2013	ፊታውራሪ አባይነህ
4	ኢንዲያና	82	20/02/2013	ኢንዲያና
5	ቱሉዲምቱ	188	21/02/2013	ቱሉዲምቱ
6	አቃቂ ሌስፔራንስ	39	21/02/2013	አቃቂ ሌስፔራንስ
7	አቃቂ አድቬንትስት	230	23/02/2013	አቃቂ አድቬንትስት
8	ኢትዮ ብሄራዊ	179	24/02/2013	ኢትዮ ብሄራዊ
9	ሲያትል	23	24/02/2013	ሲያትል
10	ቡልቡላ	150	25/02/2013	ቡልቡላ
11	ስኩል ኦፍ አይጎዳ	130	25/02/2013	ስኩል ኦፍ አይጎዳ
12	አዲስ አበባ ማረሚያ	8	26/02/2013	አዲስ አበባ ማረሚያ
13	የግል ተፈታኞች		ከ 27-30/02/2013	ክ/ከተማ ት/ጽ/ቤት

ማሳሰቢያ፡-

- ተማሪዎች ለምዝገባ ከተቀመጠው ቀን ውጭ መመዝገብ ስለማይችሉ ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎቻችሁ አስፈላጊውን ዝግጅት እንደያደርጉ እንድታሳውቁ እናሳስባለን።
- ትምህርት ቤቶችም ከታች ባያያዝነው የምዝገባ ዝግጅት ሰነድ መሰረት አስፈላጊውን ዝግጅት አድርገችሁ እንድትጠብቁ እናሳስባለን።
- የግል ተፈታኞች ከዚህ በፊት የተመዘገቡ ሆነ ምዝገባው ያለፋቸው ከጥቅምት 27 እስከ ጥቅምት 30 2013 ዓ.ም በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ት/ጽ/ቤት አስፈላጊውን መረጃ በመያዝ እንዲሁም ክፍያ የከፈላችሁበትን ደረሰኝ በመያዝ በተገለፀው ቀንና ቦታ እንድትመዘገቡ እያሳወቅን ከተገለፀው ቀን ውጭ የማናስተናግድ መሆኑን እንገለፃለን።ትምህርት ቤቶችም ለግል ተፈታኞች በማስታወቂያ እንድትገልፁላቸው እናሳስባለን።
- በምዝገባው የሚካተቱት ከዚህ በፊት የተመዘገቡት ተማሪዎች ብቻ ይሆናሉ።

የምዝገባ ፕሮቶኮል

ቅድመ ምዝገባ

መመዝገቢያ ቦታ ስለማዘጋጀት

- ለምዝገባ የኤሌክትሪክ ሀይል ማግኘት የሚቻልበትና በቂ ብርሃን ያለው ክፍል መዘጋጀት ይኖርበታል
- የመመዝገቢ ኪቱን በበቂ ሁኔታ ሊያስቀምጥ የሚችል ጠረጴዛ ሊኖር ይገባል
- የተማሪዎችን ፎቶ ለመውሰድ የምንጠቀምበት ቦታ ጀርባው (Background) ነጭ እና ተመዝጋቢው ፊቱን ወደ ብርሀን ማድረግ በሚያስችልበት ሁኔታ መዘጋጀት ይኖርበታል
- ያለንበት ወቅት በኮቪድ ምክንያት ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ስለሚገባ
    - ወደ መመዝገቢያው ክፍል የሚገባ ተመዝጋቢም ሆነ መዝጋቢ እጃቸውን መታጠብ የሚችሉበት መታጠቢያ በመግቢያው አቅራቢያ መዘጋጀት አለበት
    - ሳኒታይዘርና አልኮል በምዝገባ ክፍል ውስጥ ቀድሞ ሊኖሩ ይገባል
- የመመዝገቢያ እቃዎችን ለማፅዳት የሚያስፈልጉ ግብአቶች (ብናኝ የሌለው ጨርቅ ወይም ሶፍት) ሊዘጋጅ ይገባል
- ተፈታኞች የተመደበላቸውን የምዝገባ ቀን ቀድመው እንዲያውቁ መደረግና በተራቸው መገኘታቸውን መከታተል ያስፈልጋል (ምክንያቱም መዘጋቢው ከት/ቤቱ ከለቀቀ በኋላ ምዝገባ ማካሄድ ስለማይቻል)
- የተፈታኞችን መረጃ በግልፅ ማየት በሚያስችል መልኩ በአንድ ወረቀት የአንድ ተፈታኝ መረጃ በ 20 Font Size and 12 Line Spacing ተዘጋጅቶ መጠበቅ ይመከራል

ለምዝገባው እገዛ የሚያደርጉ ረዳቶችን ስለማዘጋጀት

- ኮቪድን ከመከላከል አንፃር ተመዝጋቢዎች ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረጋቸውን የሚከታተል ለምሳሌ፦
    - ተማሪዎች እጃቸውን በአግባቡ እንዲታጠቡ ማድረግ እና በተለይም አሻራ ለመውሰድ ያመች ዘንድ በአግባቡ በሶፍት ማድረቃቸውን የሚከታተል
    - ተማሪዎች በተወሰነ ቁጥር በመከፋፈል ወደ ምዝገባ ቦታ ማቅረብ (ከ 5 ባለበለጠ)
    - የምዝገባ ተራቸው ሲደርስ የአፍ መሸፈኛ ጭንብል በአግባቡና በተገቢው ቦታ እንዲያወልቁ ማድረግ
- የተመዝጋቢዎች መረጃ ከስህተት የፀዳ መሆኑን የሚከታተልና በተማሪ ሊስት መሰረት መዝጋቢውን የሚያግዝ(ዙ)

በምዝገባ ወቅት

የምዝገባ ኪቱን ስለማዘጋጀት

- የምዝገባ ኪት አቃዎችን በሚሰጠው ስልጠና መሰረት ከኬዙ ማውጣትና ማዘጋጀት በአካባቢውም ማንኛውም ፈሳሽ እንዳይኖር መጠንቀቅ
- የመመዝገቢያ Biometrics Devices የተሰካባትን ሃብ በስልጠናው መሰረት ኮኔክተሩን ለማራዘም ቀልም የተደረገባቸውን አቅጣጫዎች በተመሳሳይ በኩል ማድርግ ያስፈልጋል
- ላፕቶፑን ከማስነሳት በፊት ሃቡን ከላፕቶፑ ጋ ማገናኘት
- ላፕቶፑን ማስነሳትና ተገቢውን ፓስዎርድ ማስገባት
- ቢያንስ ለ 10 ያህል ደቂቃዎች መጠበቅና የምዝገባውን አፕሊኬሽን ማስነሳት (ETH Exam User Registration) (ከበስተኋላ መነሳት ያለባቸው ሌሎች አፕሊኬሽኖች እስኪነሱ ለመጠበቅ)

- የምዝገባ አፕሊኬሽኑን በምናስነሳት ሰህተት በብራውዘሩ ላይ ቀይ Background ያለው Message ካጋጠመ ብራውዘሩን መዝጋትና ላፕቶፑን Restart ማድረግ
- አፕሊኬሽኑ በሚጀምርበት ወቅት አብሮ የሚከፈተው የኮማንድ ፕሮምፕት (Command Prompt) መስኮት መዘጋት የለበትም
- የመመዝገቢያ አፕሊኬሽኑ ከተነሳ በኋላ በአፕልኬሽኑ ዊንዶው በስተቀኝ በኩል ካሉት አማራጮች Reset Hardware and Bootstrap የሚሉትን አማራጮች መንካት የለብንም

ማሳሰቢያ፦

- የመመዝገቢያ ኪቱን ጎማውን በመጠቀም ለመንተት እንዳይሞክር (በውስጡ ሊሰበሩ የሚችሉ እቃዎች ስለሚገኙ)
- ከምዝገባ ኪቱ ከሚወጡ መሳሪያዎች ውጪ ምንም አይነት መሳሪያ ከላፕቶፑ ጋርም ሆነ ከሃቡ ጋር ማገናኘት በጥብቅ የተከለከለ ነው
- በማንኛውም ወቅት ላፕቶፑን ከማንኛውም ኔትዎርክ ወይም ዋይፋይ ጋር ማገናኘት በጥብቅ የተከለከለ ነው
- የምዝገባ አፕሊኬሽኑ የሚሰራው በ Chrome Browser ብቻ ስለሆነ መቀየር የለበትም

የተመዝጋቢ ዲሞግራፊክ መረጃ ሲወሰድ

- የገቡት መረጃዎች በስትክክል መግባታቸውን ከተመዝጋቢው ፊት አረጋግጦ መቀጠል ይገባል
- ማንኛውመ ስም በምህፃረ ቃል መፃፍ የለበትም
- የትውልድ ቀን ሲፃፍ ቀን/ወር/ዓመተ ምህረት ብቻ መጠቀም ይኖርብናል
- ጳጉሜ 6 በምናስገባበት ጊዜ ስህተት ካጋጠመን ወይንም አልቀበል ካለን ዓመተ ምህረቱን ማረጋገጥ አለብን
- የአካል ጉዳትን እና የአይነስውራንን መረጃ በስትክክል መመረጡን ማረጋገጥ ይገባል

የትምህርት አይነት በሚመረጥበት ወቅት

- የሚመረጠው በ Stream (Natural Science or Social Science) ነው
- ተመዘጋቢው አይነስውር ከሆነ አፕልኬሽኑ በራሱ ስለሚመርጥ የምንመርጠው አይኖረንም

የተመዝጋቢ ፎቶ በሚወሰድበት ወቅት

- በቂ ብርሀን ማግኘት በሚቻልበት ሁኔታ የካሜራውን መብራት መጠቀም አይመከርም
- ካሜራውን ለማንቀሳቀስ ስክሩውን ከአንድ ግዜ በላይ አለማዞር (በተለይ እስከ መጨረሻ አለማዞር)
- ተመዝጋቢው መነፅርም ሆነ ማስክ ማድረግ የለበትም
- ተመዝጋቢው ቀጥ ብሎና በጣም ወደ ካሜራው ሳይቀርብ ሳይርቅም በማንዋሉ መሰረት መነሳት አለበት
- አይን በተገቢው መጠን መከፈት አለበት (ለአይነስውራን ካልሆነ በስቀር የተከደነ አይን አይቀበልም)
- አፕሊኬሽኑ በሚወስደው የምስል ባህርያት ውስጥ ቀይ የሆነ እስካለ ድረስ ምስሉን መውሰድ አይቻልም Capture Button የሚለው አይመጣም፤ ስለዚህም ተመዝጋቢው በስልጠናው መሰረት በመጠኑ እየተንቀሳቀሰ የቀዩ ምልክት እስኪጠፋ መጠበቅ ያስፈልጋል

ማሳሰቢያ፦

ፎቶው በፈተና ወቅት ተፈታኙን ለማረጋገጥ በመጀመሪያ ደረጃ የሚያገለግለ ስለሆነ ከፍተኛ ጥንቃቄ በማድረግ በጥሩ እይታና ጥራት መነሳት ይኖርበታል

የተመዝጋቢ አሻራ በሚወሰድበት ወቅት

- የአዲስ ተመዝጋቢ አሻራ ከመወሰዱ በፊት መሳሪያው በአግባቡ መፅዳት ይኖርበታል (ለኮቪድ ጥንቃቄ ብቻም ሳይሆን ያለፈው ተመዝጋቢ አሻራ ከመሳሪያው ለማፅዳት ሲባል)
- የተመዝጋቢው ጣቶች ንፁህና ደረቅ መሆን አለባቸው
- ተመዝጋቢው ከምዝገባ በፊት ሳኒታይዘር መጠቀም የለበትም (በውሃ ብቻ መታጠብ ይኖርበታል)
- ተመዝጋቢው ቆሞ አሻራ እንዲሰጥ መደረግ አለበት
- አሻራ የሚወሰደው አፕልኬሽኑ በሚሰጠው ቅደም ተከተል ማለትም መጀመሪያ የቀኝ 4 ጣቶች፣ የግራ 4 ጣቶች እና በመጨረሻም የሁለቱን እጆች አወራ ጣቶች መሆኑ መዘንጋት የለበትም
- ጣቶች ከስካነር ውጪ እንዳይሆኑ፣ እንዳይንጋደዱ እና ወደ ጎን እንዳይንቀሳቀሱ ጥንቃቄ ማድረግ
- ከጣት ጫፎች ሌላ እንዳይገባ ጥንቃቄ ማድረግ
- የጣት ጫፎች ከስካሩ መሀል እንዲያርፉ ማድረግ
- መሳሪያውን ብዙ መጫን አያስፈልግም፤ አሻራው በጣም ሲጠቁር ጥራቱ ይቀንሳል
- ምንም እንኳን 4 ጣቶች አንድ ላይ መወሰድ ቢችሉም ጣቶቻቸው የቁመት ልዩነት ያላቸው ከሆነ የየጣቶቹን አሻራ ተራ በተራ (አንድ በአንድ) መውሰድ ይመከራል
- የጎደሉ ጣቶች ወይም እጅ ሲያጋጥም በማንዋሉ መሰረት አሻራ መውሰድ (በማጥፋት)
- አሻራ ተወስዶ ሲያበቃ እጅን በቀጥታ ወደ ላይ ማንሳት ያስፈልጋል

የዐይን ብሌን ምስል በሚወሰድበት ወቅት

- ከኮቪድ ጥንቃቄ አንጻር መሳሪያውን ማጽዳት ይገባል
- መነፅር መደረግ የለበትም
- ዐይን በሰፊው መከፈት ይኖርበታል
- ስካነሩ አግድም(Horizontal) መያዝ ይኖርበታል

ዶክመንት ስካን በሚደረግበት ወቅት

- ለ 2012 ምዝገባ ዶክመንት ስካን ማድረግ ሙሉ በሙሉ መተግባር ስለማይቻል ለሁሉም ተመዝጋቢዎች (በ 2012 ምዝገባ ዶክመንት ስካን አልተደረገም የሚልና ማህተም ያለው) ወረቀት ለሁሉም ተመዘጋቢዎች ስካን ማድረግ
- ሁለት እጆቻቸውን ያጡ ተመዝጋቢዎች ሲያጋጥሙ ይህንኑ የሚጠቅስ በት/ቤቱ ዳይሬክተር ፊርማና ማህተም የተረጋገጠ መረጃ ስካን መደረግ ይኖርበታል
- ስካን ለማድረግ በምዝገባ ኪት ውስጥ የሚገኘውን ምንጣፍ በማስቀመጥ ስካን የሚደረገውን ወረቀት መጠን መርጦ (A5, A4 or A3) በትክክለኛ ቦታው ማስቀመጥ

ዳታ በማስቀመጥ ወቅት (Save and Verify)

- ስህተት አለመኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል

ማሳሰቢያ፦

- የአንድ ተመዝጋቢ መረጃ ከአንድ ግዜ በላይ እንዳይወሰድ ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል

ዳታ በሚስተካከልበት ወቅት (Data Correction)

- ዳታ ማስተካከል የሚቻለው ተመዝጋቢው በአካል በተገኘበት ብቻ ነው

ማሳሰቢያ፦

ምንም እንኳ አፕሊኬሽኑ ዳታ ለማስተካከል ቢፈቅድም ይህንን አማራጭ (Data Correction) ላለመጠቀም በቅድሚያ በመጀመሪያ የምዝገባ ወቅት Verify and Save ከማድረግ በፊት ስህተት ያለመኖሩን ማረጋገጥ ይገባል

ፓወር ሰፕላይ ባትሪ ስለመጠቀም

- መብራት በቤለበት አጋጣሚ ብቻ መጠቀም
- ባትሪው ሁል ግዜም ተሞልቶ ቻርጅ ተደርጎ እንዲቀመጥ ማድረግ
- የባትሪው ቻርጅ መጠን ከ 20% ባነሰ ወቅት አለመጠቀም
- ከባትሪው ወደ ላፕቶፕ ለማገናኘት ቁመቱ አጭር የሆነውን ኬብል ብቻ መጠቀም
- ኬብል ውስጥ ያለው ፒን ሁሌም መሀል ለመሀል መሆኑን ማረጋገጥ (ከተጣመመ እና የዳርቻውን ክፍለ ከነካ ሾርት ያደርጋል

በት/ቤት ምዝገባ ካጠናቀቀ በኋላ

- የተመዝጋቢዎቹን መረጃ ወደ HTML በመቀየር ከት/ቤቱ ር/መምህርና ከዞን የፊተና ክፍል ኃላፊ ጋር መናበብና ማረጋገጥ ይጠበቅበታል
- በስክሪን ላይ ያለን መረጃ ለመለየት ወደ ስክሪኑ ማንኛውንም ነገር ጣትንና ስክርቢቶን ጨምሮ ማስጠጋት አይፈቀድም

አጠቃላይ ማሳሰቢያ

- ምዝገባ ከሚጀመርበት ከ 16/02/2013 ጀምሮ የሙከራ (የልምምድ) መረጃ ማስገባት የተከለከለ ነው
- የልምምድ መረጃ በሚገባበት ወቅት የተመዝጋቢው ስም በ TTTT (በ 4 T) ብቻ መጀመር ይኖርበታል
- መዝጋቢውና ረዳቶቹ በማንኛውም ወቅት ማስክ ማረግ ግዴታ ነው
- በምዝገባ ወቅት ለምዝገባ የሚያስፈልጉትን ግብዓቶች ስኩል ሊስት (School List) ጨምሮ ያልተዘጋጀ ት/ምት ቤት ሲያጋጥም ጊዜ ላመቆጠብ ወደ ሌላ ት/ቤት መሄድ ይጠበቅበታል

Student Information

Study Program: Regular program ☐ Private program ☐

Name: _____

Father Name : _____

Grand Father Name: _____

Nationality: ____**Ethiopian**_____ Other _____

Date of Birth (Eth. Calendar): Date _____Month _____ YEAR _____

Gender: ☐ Male ☐ Female

Region _____ Zone _____
Woreda _____ Kebele _____

School _____

Disability: ☐ None ☐ Handicap ☐ Deaf ☐ Other

Visual Impairment ☐ None ☐ One Eye ☐ Both Eye

Phone Number_____ Email: _____

Study Stream ☐ Natural Science ☐ Social Science

Relative Information

Relation Type
(☐ Parent ☐ Adoptive Parent ☐ Grand Parent ☐ Guardian ☐ Parents Sibling)

Name _____
Father Name _____
Grand Father Name _____
Gender: ☐ Male ☐ Female

Date of Birth (Eth. Calendar): Date _____Month _____ YEAR _____

Nationality : ____Ethiopian_____(other)_____

Residence Region _____Residence Zone _____
Residence Woreda _____
Sector of Employment _____

Phone Number _____ Email: _____
sign----------